# የማኅበረ ቅዱሳን እጅግ አሳዛኝ ውድቀትና ፍጻሜ !!!

ቀቀቀቀደም ሲል በአቦይ ጳውሎስ አሁን ደግሞ በአቦይ ማትያስ የሚመራው ወያኔ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን እንዲቆጣጠርና ፀረ ቤተክርስቲያን የጥፋት ዓላማውን እንዲያስፈጽም በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሰማራውና ቤተክርስቲያንን ለ 28 ዓመት ሙሉ ቁም ስቅሏን ሲያሳያት፣ የደም ስሯን ሲቆርጥ፣ ምእመናኗን ለተኩላት በገፍ ሲያስበላ፣ ሙዳየ ምጽዋቷንና ግምጃ ቤቷን ሲዘርፍ ሲያራቁት፣ ዶግማ ቀኖና ሥርዓቷን ሲቆነጻጽልና ሲያፋልስ ባጠቃላይ ቤተክርስቲያንን ሲያወድም፣ ሲያፈርስ፣ ሲያጠፉ የኖረው የወንበዴ ቡድን መሰንበቻውን ሲዳማ ዞን ከሚሉት የደረሰውን የአብያተክርስቲያናት መቃጠልንና የምእመናን በግፍ መገደልን ተከትሎ ቡድኑ ለ 28 ዓመታት ቤተክርስቲያን በመላ ሀገሪቱ ከዚህ የከፋ ፈተና፣ አደጋና ችግር ስታሳልፍ የሚቃወሙትን ካህናትና ምእመናን እያሳፈነ ሲያሳርድ እንዳልነበረ ልክ ለቤተክርስቲያን አሳቢና ተቆርቋሪ በመምሰል አሁን የተቃውሞ እንቅስቃሴን አነሳሥቶ በፊትአውራሪነት በመምራትና ለወትሮው ባላንጣ አድርጎ የሚመለከተውን ማኅበረ ቅዱሳንን ጨምሮ ብዙዎችን ከጎኑ በማሰለፍ በአዝማችነት በአገዛዙ ላይ በማዝመት "መንግሥት በአብያተክርስቲያናትና በምእመናን ላይ በየስፍራው የሚፈጸመውን ጥቃት በቸልታ እየተመለከተ ነው፣ ወንጀለኞችን ለፍርድ አያቀርብም፣ የአብያተክርስቲያናትና የምእመናንን ደኅንነት ሊያስጠብቅ አልቻለም!" የሚል ተቃውሞ እያሰማ ይገኛል፡፡

"ታዲያ ይሄ መልካም ነው እንጅ ምን ክፋት አለው? ማኅበረ ቅዱሳንስ ለቤተክርስቲያን እንደመቆሙ በተቃውሞው ተባባሪ መሆኑ ግዴታው አይደለም ወይ?" ትሉ ይሆናል፡፡ ትክክልም ናቹህ ችግሩና እውነታው ተቃውሞው ከላይ ከላይ እንደምታዩትና እንደሚመስላቹህ ሳይሆን ድብቅ ፀረ ቤተክርስቲያን ፖለቲካዊ ዓላማ ያለው መሆኑ ነው እንጅ በትክክልም ጥያቄውና ተቃውሞው ድብቅ ዓላማ ሳያነግብ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ እንዲያውም "እጅግ ዘግይቷል!" ከማለት ውጭ የምንቃወመው ነገር ባልሆነ ነበር፡፡

የዚህ ተቃውሞ ዓላማ ሦስት ዕኩይ ዓላማዎች አሉት፡-

1ኛው. እንደምታውቁት የሲዳማ ዞን በሚሉት የደረሰውን አደጋ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ መከላከል ይቻል ነበር፡፡ ምክንያቱም አደጋው ድንገተኛ ሳይሆን በዛቻና ማስፈራሪያ ታጅቦ ቀን ተቆርጦለት ይጠበቅ የነበረና ይሄም በሚገባ የሚታወቅ ነበርና ነው፡፡ ይሁንና ግን አገዛዙ ለሲዳማዎች የክልል ጥያቄ ቀና ምላሽ መስጠት ስላልፈለገና ሲዳማዎችን በሕገወጥ እንቅስቃሴ ወንጅሎ ጥያቄያቸውን ዋጋ ማሳጣት ስለፈለገ ሆን ብሎ ወደ ጥፋት ይመራቸው ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት የጸጥታ ኃይልን አስቀድሞ በማሠማራት አደጋው እንዳይደርስ መከላከል ሲኖርበት አደጋው ደርሶ ያ ሁሉ ውድመት እስኪደርስ ድረስ የወሰደው እርምጃ አልነበረም፡፡ ጭራሽ እንዲያውም አደጋው በሚፈጸምበት ወቅት አብያተክርስቲያናትን በማቃጠልና በመዝረፉ፣ ምእመናንን በአሰቃቂ ሁኔታ በመግደሉ፣ ቤት ንብረታቸውን በመዝረፍ በማቃጠሉ የጸጥታ አካላት ከወሮበሎቹ ጋር ዋነኛ ተሳታፊና ወሮበሎቹን አሰማሪ እንደነበሩ በብዙኃን መገኛዎችን ሳይቀር የተዘገበና የሰማነው ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ቁልፉ ጉዳይ ያለው እንግዲህ እዚህ ላይ ነው፡፡ እነ አቦይ ማትያስ ይሄንን ሸፍጥ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ከዚህም በላይ ከዚህ ቀደም የደቡብ ክልል የሚሉት ባለሥልጣናት በወያኔ እየታዘዙ በቤተክርስቲያን ላይ ምን ግፍ ሲፈጽሙ እንደቆዩ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ እያወቁ ግን ቀጥተኛ ተጠያቂ ወሮበሎችንና መናፍቃኑን በመጠቀም ለዘመናት በአብያተክርስቲያናትና ምእመናን ላይ ጥቃት ሲያስፈጽም የኖረውን አገዛዙን ቀጥተኛ ተጠያቂ አድርጎ መክሰስና ማውገዝ ሲገባቸው የሲዳማን ሕዝብ ምንም በማያውቀው የወንጀሉ ፈጻሚ እንደሆነ አድርጎ በመቁጠርና በመኮነን አገዛዙ መውሰድ የነበረበትን እርምጃ ሳይወስድ ቀርቶ ሕዝቡ አደጋውን ያደረሰ አስመስለው በአገዛዙ ላይ ክስና ተቃውሞ እያሰሙ ይገኛሉ፡፡ ይሄንን የሚያደርጉበት ምክንያት ደግሞ ከላይ እንዳልኳቹህ አገዛዙ የሲዳማን የክልልነት ጥያቄ የሕዝብ ጥያቄ ሳይሆን የወሮበሎች ግርግር አስመስሎ በማቅረብ ተገቢ ምላሽ የማይገባው ሆኖ እንዲፈረጅ ለማድረግ በየአቅጣጫው ስማቸውን የማጥፋት፣ ገጽታቸውን

የማጠልሸት ዘመቻ አንዱ አካል ነው ይሄ የነ አቦይ ማትያስ የሰሞኑ እንቅስቃሴ፡፡ እንጅ ለቤተክርስቲያን በማሰብ በመቆርቆር የሚደረግ አይደለም!!!

ምክንያቱም ቤተክርስቲያን በአገዛዙ ተመሳሳይ ፖለቲካዊ ሸፍጥ ምክንያት ከዚህ የከፋ አደጋና ከባድ ሐዘን የሶማሌ ክልል በሚሉት ስታስተናግድ ይሄ ቤተክህነት ውስጥ ያለው የእነ አቦይ ማትያስ የወያኔ ቡድን እንደ ሦስተኛ አካል የሐዘን መግለጫ አውጥቶ አለፈው እንጅ የአገዛዙን ሸፍጥ በማውገዝና አገዛዙን ተጠያቂ በማድረግ ተቃውሞ አላሰማምና፡፡

ከዚያ በፊትም በርካታ ተመሳሳይ ፈተናዎች በቤተክርስቲያን ሲፈጸም ዓይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ በማሳለፍ ለአገዛዙ ተባባሪነቱን ያረጋግጣል እንጅ አንድም ነገር ብሎ አያውቅምና፡፡ ይሄ ቡድን የተቀጠረውና ሲያገለግል የኖረውም አገዛዙን እንጅ እግዚአብሔርን እንዳልሆነ ሁሉም ያውቃልና "በአገዛዙ ላይ ተቃውሞ በማሰማት የቤተክርስቲያንን ጥቅም ያስጠብቃል!" ብሎ የሚጠብቅ አንድም ምእመንም ወይም ካህን የለም!!!

2 ኛው. ዓላማ ደግሞ ወያኔ የደቡብ ክልል በሚለው የሀገራችን ክፍል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አሻራ እና የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲጠፋ በርትቶ ሲሠራ እንደመቆየቱ ይሄንንም ለማድረግ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከዚያ አካባቢ እንድትጠፋ ማድረግ የጥፋት ዓላማውን ከማስፈጸም አኳያ "ዋነኛው ተግባሬ ነው!" ብሎ ስላመነ ላለፉት 28 ዓመታት በቤተክርስቲያኗ ላይ የአካባቢው ባለሥልጣናት በርካታ በዚህ ዘመን የማይጠበቁ ግፎችን በይፋ ያለ አንዳች መሳቀቅና የተጠያቂነት ስሜት እንዲፈጸሙ ሲያደርግና በዚያ የሀገሪቱ ክፍል ቤተክርስቲያንን ሲያዳክም መቆየቱን ሁሉም ያውቃል፡፡

ይሄ የሰሞኑ ጥቃትም የዚያ ሲፈጽመው የቆየው ዕኩይ ዓላማ ቀጣይ ክፍል ነው አዲስ አይደለም፡፡ እነ አቦይ ማትያስም የሲዳማ ሕዝብ ምንም በማያውቀው እየወነጀሉ አገዛዙ እርምጃ እንዲወስድ እየወተወቱ ተቃውሞውን እያንቀሳቀሱ ያሉት የሲዳማ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጥላቻ እንዲያድርበትና ቂም እንዲቋጥር በማድረግ ለወደፊት ቤተክርስቲያንን ለጥቃት አመቻችቶ ለማስቀመጥ ነው፡፡ ይሄንን ጉዳይ በሚመለከት ማኅበረ ቅዱሳን በቴሌቪዥኑ ከሠራው ዘገባ እንደተመለከታቹህት አቦይ ማትያስ ለጦርነት ዛቻ እንደሚያሰማ የጦር መኮንን "አይችሉንም!" እስከማለት ወርደው በማስመሰል ሲቀሰቅሱና ሲዝቱ የሚታዩበት ምክንያት ይሄ ነው ሌላ አይደለም!!!

3 ኛው. ዓላማ ለዘመናት በየስፍራው በአብያተክርስቲያና፣ በምእመናንና በካህናት ላይ የሚፈጸመው ግፍ እየከፋ እየበዛ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የሕዝበ ክርስቲያኑ ብሶት ድንገት ሊገነፍል ወይም ሊፈነዳ እንደሚችል ስለፈሩ ድንገት ከመገንፈሉ ወይም ከመፈንዳቱ በፊት ፍንዳታውን ለማምከን ወይም የብሶት እምቅታውን ለማስተንፈስ ነው የዚህ የውሸት ተቃውሞ ሦስተኛው ዓላማ፡፡ ይሄንንም ዘዴ ከዚህ ቀደምም ተጠቅመውበታል፡፡

ታስታውሱ እንደሆን አቡነ ሳሙኤል ከአዜብ መስፍን ጋር በመሆን ከአባ ጳውሎስ ጋር ፍልስልስ ያለ ጠብ ውስጥ የገቡ መስለው በመተወን ይሄው አቡነ ሳሙኤል ተብየው በርካታ የደብር አለቆችን ወይም አሥተዳዳሪዎችን ከጎኑ በማሰለፍ መጨረሻ ላይ የውሸቱ ፀብ ያለ አንዳች መቋጫ ከመጠናቀቁ ማግስት ከአቡነ ሳሙኤል ጎን ተሰልፈው የነበሩት ከሰባ በላይ የደብር አለቆች ከሥራቸው እንዲባረሩ መደረጉን ታስታውሳላቹህ፡፡ የውሸቱ ፀብ ዓላማ የነበረው በወቅቱ በአባ ጳውሎስ ላይ በየስፍራው ጉምጉምታና የተቃውሞ እንቅስቃሴ ስለነበረ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎቹን ሰብስቦ ወደ አንድ ማዕከል በማምጣትና በቁጥጥር ስር አድርጎ ማምከን ነበር፡፡ ያሰቡትንም በተሳካ ሁኔታ አከናውነውታል፡፡ አቡነ ሳሙኤል ማለት በደርግ ጊዜ የመጨረሻ ዓመታት አካባቢ ገነት ሆቴል መነኩሴ መስለው ለሁለት ዓመታት ያህል ክፍል ይዘው ሲሰልሉ የነበሩ የወያኔ ታጋይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ እናም የቤተክህነቱ የወያኔ ቡድን ሰሞናዊ የውሸት የተቃውሞ እንቅስቃሴ ዓላማዎቹ እነኝህ ናቸው ሌላ አይደለም!!!

የገረመኝ ጥንቃቄን በእጅጉ የሚያበዛው ማኅበረ ቅዱሳን እነኝህ ተቃውሞውን አቀንቃኞቹ ቤተክርስቲያንን ለ 28 ዓመታት ሲነርሻት የኖረው የወያኔ ቡድን መሆናቸው ድፍረት ሰጠው መሰለኝ በዚህ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ዘሎ መግባቱ ነው፡፡ ይሄንን ባየሁ ጊዜ ማኅበረ ቅዱሳን የፈለገ ተአምር ቢፈጠር በዚህ ዓይነት የተቃውሞ እንቅስቃሴ ታይቶ አያውቅምና "ማኅበረ ቅዱሳን ከየት ብቅ አለ? በሕይዎት ነበረ እንዴ ለመሆኑ???" ነበር ያሰኘኝ፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ሰሞኑን እያደረጉ ያሉት ነገር ሁሉ እውነት ለአምልኮቱ በመቅናት፣ ለቅድስት ቤተክርስቲያን በመቆርቆር፣ ክርስቲያናዊ ግዴታን ከመወጣት አንጻር "የመጣው ይምጣ እንደ ክርስቲያንነታችን በክርስቶስ ስም እንቀበለዋለን!" በሚል

ከሆነና እንዲህ ዓይነት ቁርጠኝነት ከነበራቸው ምነው ታዲያ የወያኔ አውራ የሆነው አቦይ ስብሐት "የኦርቶዶክስንና... አከርካሪ እንዳያንሠራራ አድርገን ሠብረነዋል!" ብሎ በእርግጠኝነት፣ በልበሙሉነትና በኩራት እንዲናገር ያስቻለውን ወያኔ ከመናፍቃን ጋር በመቀናጀት ተነግሮ የማያልቅ ጥቃት በቤተክርስቲያን ላይ ሲያደርስና ቤተክርስቲያንን እንዳልሆነች አድርጎ ሲጫወትባት ያኔ የት ሔደው ነው ታዲያ ጭጭ ያሉት???

እኔ ራሴ ሳልቀር "ማኅበረ ቅዱሳን ለቤተክርስቲያን ዛሬ ያልጮኸና ያልቆመ መቸ ሊጮህና ሊቆም ነው???" እያልኩ ከቤተክርስቲያን ዐውደ ምሕረት (ማ/ስ/ቅ/ልደታ ለማርያም ቤተክርስቲያን አዲስ አበባ ከ 1993-1995 ዓ.ም.) እስከ መጽሔት ጋዜጣና ዶረ ገጾች ላይ ላንቃየ እስኪቀደድ ድረስ ከሐዋርያት እስከ ሠማዕታት፣ ከቅዱስ አትናቴዎስ እስከ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ድረስ ደም አፍስሰው አጥንት ከስክሰው ቤተክርስቲያንን እንዴት እንዳቆዩዋት በማስታወስና "ክርስቲያኖች ነን!" ካልን የአባቶቻችንን አሠረ ፍኖት መከተል የግድ መሆኑን በማሳሰብ አብዝቶ ስጮህ ማኅበረ ቅዱሳን ያኔ መቸ ነበረና ነው አሁን ቤተክርስቲያን ምእመናኗ ተግዞ ካለቀ በኋላ፣ ስሮቿ በሙሉ ተቆርጠው ከደረቀች በኋላ፣ ተነቅላ መጣል ብቻ ሲቀራት "አለን ዘራፍ!" የሚለው??? "ጅብ ከሔደ ውሻ ጮኸ!" የሚለውን ተረት ሊያስተርተን ካልሆነ በስተቀር፡፡ የዚህ እንቅስቃሴ ዓላማ ከላይ የገለጽኩላቹህ የአገዛዙን ፖለቲካዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እየተተወነ ያለ ባይሆን ኖሮ ማኅበሩ ተቃውሞው ከልቡ በቁርጠኝነት የያዘው ቢሆን የሚጠቅም እንጅ የሚጎዳ ባልሆነ ነበር፡፡

ነገር ግን በቀደሙት የቤተክርስቲያን ከባባድ ፈተናዎች ስንጮህ፣ ቤተክርስቲያን የደም እንባ ስታነባ፣ ስንት የማይጠገን ኪሳራና ጉዳት ሲደርስባት ምንም እንዳልተፈጠረ በመቁጠር ከአመራሩ እስከ አባላቱ ለየግል ሕይዎቱ፣ ደኅንነቱና ጥቅሙ በማድላት መስሎ እያደረና በዝምታ በመሸበብ "ጆሮ ዳባ ልበስ!" ብሎ አልነበረም ወይ እራሱን ደብቆ ቤተክርስቲያንን ሲያስበላ፣ ሲያስደበድብ የኖረው??? ዛሬ ከየት የመጣ ክርስትና፣ ቅናት፣ ድፍረት፣ ወኔ፣ ወንድነትና ተቆርቋሪነት ነው ይሄንን ያህል የሚያስደነፋው???

ለማየት ያብቃቹህ የእነ አቦይ ማትያስ ቡድን ዓላማውን ካሳካ በኋላ ዝም ሲል እነሱም ጭጭ ሲሉ ታዩዋቸዋላቹህ፡፡ ተቃውሞውን አይገፉበትም፡፡ ይሄንን እርግጠኛ ሆኘ እነግራቹሃለሁ፡፡ እኔ እንዲያውም ምን የሚል ጥርጣሬ አለኝ መሰላቹህ ከላይ የገለጽኩላቹህን የተቃውሞውን ፖለቲካዊ ዓላማ አውቀው አገዛዙን ለመተባበር ያደረጉት ነው የሚመስለኝ፡፡ ምክንያቱም አሁን የማኅበሩ መሥራች አባላቶቹና ማኅበሩን እንደ ማኅበር አቁመው የያዙት ዋነኛ አገልጋዮቹ በዳንኤል ክብረት ደላላነት በዐቢይ አሥተዳደር ከአንባሳደርነት እስከ የመምሪያ ኃላፊነት ተሹመው የአገዛዙ አጋር ተደርገዋልና ነው፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን የድሮው ማኅበረ ቅዱሳን ይመስላቹሃል??? ዕድሜ ለዳንኤል ክብረት አይባልም እንጅ ከፀረ ቤተክርስቲያኑ ወያኔ/ኢሕአዴግ ጉያ ውስጥ ሔዶ ተወሽቋል እኮ!!!

የሚገርማቹህ ነገር ከበፊት ጀምሮ በበረሃ ያሉ ከብቃት ደረጃ የደረሱ ቅዱሳን አባቶችን ሔጀ በማገኝበት ወይም በምጠይቅበት ወቅት አንዳቸው ብቻ እንዳይመስሏችሁ ሁሉም ልል በምችልበት ደረጃ እጅግ ግራ እስኪገባኝ ድረስ ማኅበረ ቅዱሳን ሌላው ቀርቶ ስሙ እንኳ እንዲጠራባቸው አይፈልጉም፡፡ በዚህ ምክንያት ልጠይቅ ልጎበኝ ሔጀ ሁልጊዜ ከእነሱ ጋር እየተጣላሁ ወይም አኩርፌ ነበር የምመለሰው፡፡ ለካ እነሱ የሚያዩት ፍጻሜን እንጅ ጅማሬን አይደለምና የማኅበሩን ፍጻሜ ስለሚያውቁ ኖሯል ለካ እንዲያ የሚጠሉት!!!

እኔ ይሄንን ስለማላውቅ "እንዴ! ምንድን ነው የምትሉት? ማኅበረ ቅዱሳን ባይኖርና ወጣቱን እስከ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ ባይይዘው ኖሮ እንደ መናፍቃንና እንደ ወያኔ የተቀናጀና የተባበረ ጥረት ቢሆን ቤተክርስቲያን ደብዛዋ ጠፍቶ አልነበረም ወይ? እንዴት ማኅበረ ቅዱሳንን በክፉ ታዩታላቹህ???" እያልኩ ያለ አቅሜ ሽቅብ በእነሱ ላይ እየጮህኩና እየተነጫነጭኩ ከእነሱ ጋራ እጣላ ነበር፡፡ ምክንያታቸው የገባኝ አሁን የወያኔ ለውጥ የሚባለው ድራማ መጥቶ ሲተወንና ወያኔ በዚህ ድራማው ተቃዋሚዎችን ብቻ ሳይሆን ማኅበረ ቅዱሳንን ሳይቀር ከጉያው ወሽቆ አገልጋዩ ሲያደርገው ነው የገባኝ!!!

እኔ ደግሞ ይገርማቹሃል ነፍስ ያላቸው ሰዎች መስለውኝ ለውጥ የሚባለው የወያኔ የማጃጃያ ድራማ መተወን እንደጀመረ በድራማው ሳቢያ የተፈጠረውን ክፍተት ለመጠቀም በማሰብ "አሁን ይደፍሩ ይሆናል!" ብየ ተስፋ በማድረግ ከማኅበሩ ሰዎች ከዋነኞቹ አንዱን ቀጥሬ በማነጋገር "ፖለቲካል ፓዎር (ሥልጣን) ሳይኖር ሳይያዝ ዳር ተመልካች ተሁኖ የቤተክርስቲያንንም ሆነ የሀገሪቱን ጥቅም ማስጠበቅና ከጥቃት ከጥፋትም መከላከል መጠበቅ ፈጽሞ አይቻልምና

የተወሰናቹህት ማኅበሩን ለቃቹህ ውጡና አጋጣሚውን ተጠቅመን የሀገር አንድነትንና ህልውናን ፈጽሞ ለድርድር የማያቀርብ፣ ብዝኃነትን (diversity) የሚያስተናግድ፣ በዘር ላይ ያልተመሠረተ ራስን በራስ የማሥተዳደር መብትን (federation) የሚያሰፍን ወይም የሚያቀነቅን ፓርቲ እንመሥርት? በማኅበረ ቅዱሳንነታቹህ የምትታወቁ መሆናቹህ አያሥጋቹህ፡፡ እራሱ ዐቢይ ከየት እንደመጣና ማንን እንደሚወክል ማየት ትችላላቹህ፡፡

ዐቢይ ብቻ አይደለም በርካታ መናፍቃን የመንግሥት ሥልጣንን የተቆጣጠሩበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ይሄ ከፍተኛ አደጋ አለው፡፡ ስለሆነም ለመናፍቃኑ ነውር ያልሆነ ነገር ለእኛ ተለይቶ ነውር የሚሆንበት ምንም ምክንያት የለምና እኛም በፖለቲካው እንሳተፍ፡፡ አብሶ ደግሞ ሲሦ መንግሥት ይዛ የሀገሪቱን የመንግሥት አሥተዳደርና ሥርዓት ለማቅናት ስትፈጋ፣ ስትማስን፣ ስትደክም ለኖረች ለእኛ ቤተክርስቲያን 'ፖለቲካና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸውና በፖለቲካ ጉዳይ አያገባንም!' የሚለውን እኛን በዘዴ ከፖለቲካው ለማራቅ የተዘየደን ሽፍጠኛ አባባል በመቀበል ከፖለቲካው መራቅ ሲበዛ አላዋቂነትና ተላላነት ከመሆኑም በላይ የቤተክርስቲያንን አደራ መብላት ነው፣ መናፍቃንና እስላሞች የመንግሥትን ሥልጣን ተቆጣጥረው እንዲጫወቱብንና እንዲያጠፉንም መፍቀድ ነው!!!

ትናንትና መናፍቃንና እስላሞች ኢሕአዴግ ውስጥ በመግባት ጥቅሞቻቸውን ሲያስከብሩ ያዩ ወንድሞች 'እኛም ብንገባ የቤተክርስቲያንን ጥቅም እናስከብራለን!' ብለው ገብተው የሀገርንና የቤተክርስቲያንን ጥቅም ማስከበር፣ ከጥቃት መከላከል ፈጽሞ እንዳልቻሉ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም የአገዛዙ ርዕዮተዓለም፣ ዓላማና መሠረተ እምነት ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ቤተክርስቲያን በመሆኑ አገዛዙ የሚመቸው ለመናፍቃኑና ለእስላሞቹ እንጅ ለእኛ ባለመሆኑ ነው፡፡ ይሄ መንገድ ዝግ ከሆነ መሞከር ያለብን ፓርቲ በማቋቋም ሥልጣን መያዝ ብቻ ነው፡፡ የምንናቋቁመው ፓርቲ ለአንድ ሃይማኖት ብቻ የቆመ እንዳይመስል በኢትዮጵያዊነትና ለኢትዮጵያዊ እሴቶች መጠበቅ ቀናኢ፣ ተቆርቋሪ የሆኑ የእስልምናና የፕሮቴስታንት ተከታዮችን እናካትታለን........!!!" ብየ ጠይቄያቸው ነበር፡፡

"እሽ ላማከራቸውና መልሱን እነግርሃለሁ!" ብሎኝ ተለያየን፡፡ በቀጠሮ ስንገናኝ "የፓርቲዎች ቁጥር በርክቷል በዚህ ቁጥር ላይ ተጨማሪ ከመሆንና የፓርቲ ቁጥርን ይበልጥ ከምናበራክት ያሉትን ብናይ የተሻለ ነው!" የሚል መልስ ይዞ መጣ፡፡ እኔም እስኪ አሉ ከምትሏቸው ፓርቲዎች አንድ እንኳ ለሀገሪቱ ታሪክ፣ መለያ፣ ማንነት፣ መገለጫ፣ እሴቶች መጠበቅና መከበር የጸና አቋም ያለውን አንድ ፓርቲ እንኳን ጥቀስልኝ ማን አለ??? ሁሉም ዕይታ አስተሳሰባቸው ከ ያ ትውልድ ፀረ ኢትዮጵያዊ እሴቶች ዕይታና ቅኝት የተቀዱ አይደሉም ወይ? እስኪ ደኅና የምትለውን አንድ እንኳ ጥቀስልኝ???" አልኩት፡፡ አንድም ሊጠቅስልኝ አልቻለም፡፡ ይሄንን ብሎ እንዲያግባባቸው መልሽ ላኩት፡፡ ከሦስት አራት ቀናት በኋላ ስደውልለት "ስብሰባ ላይ ነኝ በአንተ ጉዳይ ላይ እየተነጋገርን ነው በኋላ እደውልልሀለሁ!" አለኝ፡፡

ብጠብቅ የለም፡፡ ሳምንት አለፈና ደወልኩ፡፡ ከሀገር ውጭ ጉዞ ነበረውና ሲመለስ እንደሚደውልልኝ ነገረኝ፡፡ ሳይደውል ስለቀረ ከወር በኋላ ደወልኩለት፡፡ ምቹ ሁኔታ ላይ እንዳልሆነና እንደሚደውልልኝ ነገረኝ፡፡ ይሄም ደግሞ ተደጋገመ፡፡ "በቃ እነኝህ ሰዎች አልፈለጉም ማለት ነው!" አልኩና ተውኩት፡፡ ያንን ሁሉ አስረድቸ ጊዜውን ባለመረዳታቸው፣ ሀገርና ቤተክርስቲያን የተጋረጠባቸውን አደጋ ባለመገንዘባቸው በእጅጉ አዘንኩ!!!

እሱም ሳይደውል በዚያው ቀልጦ ቀረ፡፡ ዛሬ ይሄው እንደምታዩዋቸው ከፊሎቹ በየቦታው በአንባሳደርነትና በሥራ ኃላፊነት በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተሹመው ወያኔ/ኢሕአዴግን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ልክ እንደ ሚያገለግሉት ወያኔ/ኢሕአዴግ ሁሉ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ ቤተክርስቲያን ሆነዋል ማለት ነው፡፡ አያሳዝኑም??? ቆይ እንዲያውም ይሄንን የሚያረጋግጥ በቴሌቪዥናቸው ያስተላለፉትን ዝግጅት በሌላ ጽሑፉ እመለስበትና አሳያቹሃለሁ፡፡ የማኅበረ ቅዱሳን መጨረሻ እንዲህ ይሆናል ብላቹህ አስባቹህ ታውቃላቹህ??? የት ይደርሳል የተባለ ምን የት ተገኘ ነበር የተባለው??? እጅግ ያሳዝናል!!! ነፍስ ይማር ማኅበረ ቅዱሳን!!!

ድል ለቤተክርስቲያን!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com